ሚኔሶታ፡ የጤና፡ ክፍል፡ ትክክለኛ፡ መረጃ (Minnesota Department of Health)

# የነቀርሳ፡ የቆዳ፡ ምርመራ (ማንቱ)

የነቀርሳ፡(ቲቢ)፡ የቆዳ፡ምርመራ፡አንድ፡አንድ፡ጊዜም “ማንቱ”ተብሎ፡የሚጠራው፡ ቀላልና፡ጉዳት፡የማያደርስ፡ ድብቅ፡ነቀርሳ፡መኖሩንና፡አለመኖሩን፡ለማወቅ፡የሚደረግ፡ ምርመራ፡ነው።



## ድብቅ፡ ነቀርሳ፡ በሽታ፡ምንድነው?

ነቀርሳ፡ሁለት፡ደረጃዎች፡አሉት። ሁለቱም፡ደረጃዎች፡ በመድሃኒት፡ሊድኑ፡ይችላሉ።
የነቀርሳ፡ጀርሞች፡ሰዉነትዎ፡ዉስጥ፡ለመጀመሪያ፡ጊዜ፡ሲገቡ፡ ድብቅ፡ ነቀርሳ፡ ይፈጥራሉ።
ድብቅ፡ ነቀርሳ፡ ሕክምና፡ ካልተደረገለት፡ ወደ፡ ሳንባ፡ ነቀርሳ፡ በሽታ፡ ተቀይሮ፡ ከአንድ፡ ሰው፡ ወደ፡ ሌላ፡ በአየር፡ ሊሰራጭ፡ ይችላል።

| አንደኛ፡ ደረጃ<br>ድብቅ፡ ነቀርሳ | ሁለተኛ፡ደረጃ<br>ንቁ፡ ነቀርሳ፡ በሽታ |
|---|---|
| የነቀርሳ፡ጀርሞች፡ ሰውነትዎ፡ ውስጥ፡ተኝተዋል። ይህ፡ ደርጃ፡ለረጅም፡ጊዜ፡ሊቆይ፡ይችላል (እስከ፡ብዙ፡ዓመታት)። | የነቀርሳ፡ጀርሞች፡ነቅተዉ፡የአካል፡ክፍሎችን፡አየጎዱ፡ይሄዳሉ። |
| የሕመምተኛ፡መልክ፡ ወይም፡ ስሜት አይኖርቦትም።<br>የደረትዎ፡ኤክስረይ፡ዉጤት፡ ንፁህ፡ ሆኖ፡ ይታያል። | ሕመም፡ ይሰማዎታል።<br>ዶክቶርዎ፡ ነቀርሳው፡ምንዎን፡ እንደጎዳ፡<br>ለማወቅ፡ልዩ፡ ምርመራ ያደርጋል።. |
| በሽታውን፡ ለሌሎች፡ ሰዎች፡ አያሰራጩም። | የነቀርሳ፡ጀርሞቹ፡ ሳንባዎ፡ውስጥ፡ካሉ፡በሽታውን፡ በሳል፣ በማስነጠስ፣ በንግግር፡ወይም፣ በመዝፈን፡ ሊያሰራጩት፡ይችላሉ።. |
| ባብዛኛው፡ለዘጠኝ፡ወር፡መድሃኒት ፡በመዉሰድ፡ማከም፡ይቻለል። | ቢያንስ፡ለ6፡ወራት፡ያህል፡3 ወይም፡4፡መድሃኒቶች፡ በመዉሰድ ይድናል |

## ድብቅ፡ነቀርሳ፡እንዳለብኝ፡እንዴት፡አዉቃለሁ?

የነቀርሳ፡የቆዳ፡ምርመራ(ማንቱ)ድብቅ፡ነቀርሳ፡በሽታ፡እንዳልዎት፡ማሳወቅ፡ይችላል። ከሳንባ፡ነቀርሳ፡በሽትኛ፡ አጠገብ፡ከሆናችሁ፡ድብቅ፡ነቀርሳ፡ሊተላለፍቦት፡ይችላል (በሽተኛ፡መሆናቸውንም፡ባታዉቁ)

ሐኪምዎ፡በትንሽ፡የምርመራ፡መርፌ፡ጉዳት፡የማያደርስ፡ ፈሳሽ(ቱበርኩሊን፡የሚባል)፡ከቆዳዎ፡ሥር፡ክንድዎ፡ላይ፡ ይወጋዎታል።



## ምንም፡እንኳን፡ለእርስዎ፡ደህና፡ሆኖ፡ቢታይም፡ ሐኪምዎ፡ የቆዳዉ፡ምርመራ፡ከተደረገ፡ከ2፡ ወይም ከ3፡ቀን፡በኋላ፡ክንድዎን፡ማየት፡አለበት።

መደሃኒቱ፡ካልተስማማዎት፡አበጥ፡ይላል።
ሐኪምዎ፡እብጠቱን፡ይለካዋል።
እብጠቱ፡ጥቂት፡ሳምንታት፡ቆይቶ፡ይጠፋል።

## ከምርመራው፡በኋላ፡ክንዴን፡እንዴት፡አድርጌ፡ ልጠብቅ?

- ክንድዎን፡በሻሽ፡ወይም፡በፕላስተር፡አይሸፍኑ
- ክንድዎን፡ከማሸት፡ወይም፡ከማከክ፡ይጠንቀቁ
- ቦታዉ፡ካሳከክወት፡ቀዝቃዛ፡ጨርቅ፡ ያድርጉበት።
- ክንድዎን፡ማጠብ፡ይችላሉ፡ግን፡ተጠንቅቀው፡ ያድርቁት።

# የነቀርሳ፡ የቆዳ፡ ምርመራ(ማንቱ) - ገፅ 2

**የነቀርሳ፡ ምርመራን፡ አይፍሩ። ነቀርሳ፡ሊድን፡ይችላል!**

## ከምርመራው፡ነፃ፡ከሆኑስ?

ፈሳሹ፡የተወጋችሁበት፡ቦታ:በጣም፡ትንሽ፡እብጠት፡ወይም ጨርሶ፡እብጠት፡ከሌለበት፡ምርመራው፡"ንፁህ" ነው። ነቀርሳ፡የለባችሁም፡ ማለት፡ነው። በአንድ፡አንድ፡ሁኔታ፡ወደፊት፡ሌላ፡ምርመራ፡ ያስፈልጋችሁ፡ይሆናል።

## ምርመራው፡እርግጠኛ፡ከሆነስ ?

ምርመራው፡እርግጠኛ፡የሚሆነው፡ፈሳሹ፡የተወጋበት፡ቦታ፡ ላይ፡የተወሰነ፡ስፋት፡ያለው፡እብጠት፡ካለ፡ነው። ይህ፡ሲሆን፡የነቀርሳ፡ጀርሞች፡ሰውነትዎ፡ውስጥ፡አሉ፡ ማለት፡ሊሆን፡ይችላል።
አብዛኞቹ፡እርግጠኛ፡የቆዳ፡ምርመራ፡ውጤት፡ ያላቸው፡ሰዎች፡ድብቅ፡ነቀርሳ፡አላቸው።
ለማረጋገጥ፡ዶክተር፡መርምሮ፡የደረት፡ኤክስሬይ፡ያደርግ ልዎታል።
ሌላ፡ዓይነት፡ምርመራም፡የሳንባ፡ነቀርሳ፡ካልዎት ለማረጋገጥ፡ይቻላል።

**የራስዎን፡ጤናና፡የቤተሰብዎን፡ጤና፡ይጠብቁ - የቆዳ፡ነቀርሳ፡ምርመራ፡ያድርጉ!!**
የነቀርሳ፡ምርመራውን፡ለማድርግ፡ዶክተርዎን፡ወይ ም፡ይሕዝብ፡ ጤንነት፡ክፈል፡ይጠይቁ።.

## የነቀርሳ፡ምርመራ፡አስፍላጊ፡የሚሆንበት፡ ሁኔታ፦

- ከነቀርሳ፡በሽተኛ፡አጠገብ፡ከሆኑ፡ወይም፡ብዙ፡ግን ኙነት፡ከኖራችሁ
- የነቀርሳ፡በሽተኞች፡በብዛት፡ያሉበት፡አገር፡ከኖሩ
- የጡረታ፡ቤት፤ክሊኒክ፤ሆስፒታል፤እስር፡ቤት፡ ቤት፡የሌላችው፡መጠግያ፡ሠራተኛ፡ወይም ነዋሪ፡ከሆኑ፡ ወይም
- የኤቸአይቪ፡በሽታ፡ ወይም፡አንድ፡አንድ፡ዓይነት የጤና፡ችግር፡ ካላችሁ።

## ቢሲጂ(የነቀርሳ፡ክትባት) ከተከተብኩስ ?

ቢሲጂ፡ክትባት፡ከተከተባችሁ፡የቆዳ፡ምርመራ፡ማድረግ፡ት ችላላችሁ።

- ቢሲጂ፡ክትባት፡ያላቸው፡ሰዎች፡የሳንባ፡ወይም፡ ድብቅ፡ነቀርሳ፡ሊኖራቸው፡ይችላል
- ቢሲጂ፡ክትባት፡ሕፃናት፡በነቀርሳ፡በሽታ፡በጣም እንዳይታመሙ፡ይከላከላል።ሰው፡እያደገ፡ሲሄድ፡ ግን፡መከላከያው፡እየጠፋ፡ይሄዳል
- አንድ፡አንድ፡ጊዜም፡ቢሲጂ፡ክትባት፡እርግጠኛ፡ የነቀርሳ፡የቆዳ፡ምርመራ፡ውጤት፡ያሳያል።የቆዳ ውን፡ምርመራ፡ሲያደርጉ፡እርግጠኛ፡ውጤት፡ካል ዎት፡ከቢሲጂ፡ክትባቱ፡ሳይሆን፡ሰውነትዎ፡ውስጥ፡ካ ሉት፡የነቀርሳ፡ጀርሞች፡ሊሆን፡ይችላል

**ቢሲጂ፡ክትባት፡ቢኖራችሁም፡የነቀርሳ፡የቆዳ፡ምርመራ፡ ማድርግ፡ይችላሉ!!**

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Tuberculosis Prevention and Control Program
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/tb